# 2. የሰው ግድያ ወንጀል፡ የወንጀሉ ነባራዊ ሁኔታ፣ አፈጻጸምና ምክንያቶች በምስራቅ ጎጃምዞን አማራ ክልል፤ ኢትዮጵያ


## 1አለሜ ሁሜኣት 2አንተነህ ገረሜው1አለሙታዬ

1. የህግ ትምህርት ቤት፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ ኢትዮጵያ
2. የህግ ትምህርት ቤት፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ ኢትዮጵያ
3. የህግ ትምህርት ቤት፣ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ፣ ኢትዮጵያ



***አፅርኦተ-ፅሁፍ***

*የግለሰቦች በህይወት የመኖር መብት በተለያዩ የዓለምአቀፍ፣ አህጉራዊ እና ሀገራዊ የሰብዐዊ መብት ቃልኪዳኖች ላይ እውቅና እውቅና ያገኘ ማስረታዊ ሰብዐዊ መብት ነው፡ የዚህ መብት ጋሬጣ ከሆኑ ድርጊቶች አንዱ በግለሰቦች የሚፈፀም የሰው መግደል ወንጀል ምክንያቶች ከማህበረሰቡ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ አንፃር ይለያያሉ፡፡ በምስራቅ ጎጃም ዞን ባለፉት ስድስት አመታት 914 የሰውግድያ ድርጊቶች ተፈፀመዋል፡፡ የዞኑ ፖሊስ መምሪያ ለዚህ ከፍተኛ የሰው መግደል ወንጀል መንስኤዎችና ምቹ ሁኔታዎችን በመመርመር አስፈላጊ የሆኑ የህግ፣ አስተዳደራዊ እና ተቋማዊ እርምጃዎችን የሚጠቁም ጥናት እንዲሰራለት ደብረማርቆስ ዩነቨርሲቲን በጠየቀው መሰረት ይህ ጥናት ተሰርቷል፡፡ ጥናቱ በዞኑ ካሉ 20 ወረዳዎች 5 ወረዳዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን እነዚህም በስድስት አመት ውስጥ ከፍተኛ የሰው መግደል ወንጀል ያስተናገዱ ናቸው፡ ጥናቱ ማጠናዊና አይነታዊ የጥናት ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን በጥናቱ ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም ውሳኔ ያገኙ100 የሰውግድያ መዛገቦችን ላይ ማጠናዊ የመረጃ ማሰብሰቢያ በማጠቀም መረጃ ተሰብስቧል፡፡ እንዲሁም ደግሞ አይነታዊ የመረጃ ማሰብሰቢያ በማጠቀምከአቃቤ ህጎች፣ ዳኞች እና የህግ ታራሚዎች ጋር ቃለ ማጠይቅ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ከሟች ቤተሰቦች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች፣ ከፖሊስ፣ ከማህበረሰብ ተወካዮች፣ ከወረዳ ሚሊሽያ ተወካዮች፣ ከአስተዳደርና ፀጥታ ተወካዮች፣ ከሜሬት አስተዳደር ተወካዮች፣ ከሚሚያ ቤት አስተዳደር እና ከሴቶችና ህፃናት ፅ/ቤት ተወካዮች ጋር ቡድን ተኮር ውይይቶች ተደርገዋል፡፡ የትናቱ ዉጤ እንደሚያሳየዉ በዞኑ*


---

*ከሚፈፀሙግድያዎች 49 በመቶ በሸሜ የሚፈፀምሲሆን ጅንፍ በማል የሚታወቀውበሸሜ ጨፌ ላይ የሚከለቀውየብረት ማጠናከሪያ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው፡ በተለየ ትኩረት የሚኙ የግድያ አይነቶች በቡድን የሚፈፀሙግድያዎች እና በቤተሰብ መሀከል የሚፈፀሙ ግድያዎች እንደሆኑ ጥነ ቱ ያሳያል፡፡ ግምገር ቀደም የግድያ መንስኤዎች ድንገተኛ እና እለታዊ ግጭት፣ የሚሬት ግጭት፣ ቂምበቀል እና ደካማየፍትህ ስርዐት እንደሆኑ ተለይተዋል፡፡ የሚሬት አስተዳደርን ማሻሻል፣ የግጭት አስወጋጅ አደረጃጀቶችን እና የሀይማኖት አባቶች ሚናን ማጎደግ ብሎምየፖሊስ መዋቅርን ማጠናከር ችግሩን ለመቀነስ የሚረዱ ዋነኛ የመፍትሄ ሀሳቦች ናቸው፡*

*ቁልፍ ቃላት፡- ሰውመግደል፣ የሚሬት ግጭት፣ በቀል፣ ሀይማኖት እና ወንጀል*

## 1. የሰውመግደል ወንጀል በምስራቅ ጎጃምዞን

### 1.1. በምስራቅ ጎጃምዞን የስድስት አመት የሰውመግደል ወንጀል አሀዛዊ መረጃ

በምስራቅ ጎጃምዞን ባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ ያለውየሰውግድያ ወንጀል ማጠን አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ እያለ የሚታይ ነው፡ በአንድ ዓመት የሚቀንስበት ሁኔታ ከዚያምበሌላኛውዓመት ደግሞየሚጨምርበት ሁኔታ አለ፡፡ ከዞኑ ፖሊስ መምሪያ በተገኘ መረጃ ማስረት ከ2005 እስከ 2010 ዓ.ም ባሉት ስድስት አመታት ብቻ 914 የሰውግድያ ድርጊቶች ተፈፅመዋል፡፡ ይህምማለት በየአመቱ በአማካይ 152 ሰዎች በሰው ይገደላሉ፡፡ የሚከተለው ሰንጠረዥ በ20 የዞኑ ወረዳዎችና ከተሞች ባለፉት ስድስት አመታት የነበረውን የሰውግድያ ማጠን የሚያሳይ ነው፡

| ተ.ቁ | ወረዳ/ከተማ | 2005 | 2006 | 2007 | 2008 | 2009 | 2010 | ድምር | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **1** | ቢቡኝ | 8 | 8 | 2 | 5 | 2 | 3 | **28** | **16ኛ** |
| **2** | ስናን | 5 | 4 | 8 | 4 | 4 | 3 | **28** | **16ኛ** |
| **3** | ጎዛምን | 14 | 10 | 17 | 17 | 13 | 14 | **85** | **1ኛ** |
| **4** | ማቻከል | 8 | 10 | 11 | 5 | 15 | 6 | **55** | **7ኛ** |
| **5** | ደብረኤልያስ | 11 | 4 | 8 | 5 | 5 | 8 | **41** | **12ኛ** |
| **6** | ባሶሊበን | 15 | 13 | 16 | 8 | 16 | 16 | **84** | **2ኛ** |
| **7** | አዋበል | 9 | 5 | 12 | 2 | 8 | 6 | **42** | **11ኛ** |
| **8** | አነደድ | 10 | 5 | 3 | 7 | 4 | 3 | **32** | **15ኛ** |
| **9** | ደባይ | 10 | 5 | 3 | 6 | 7 | 10 | **41** | **12ኛ** |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **10** | ደጀን | 2 | 9 | 10 | 6 | 13 | 15 | **55** | **7ኛ** |
| **11** | እነ ማይ | 6 | 7 | 10 | 12 | 13 | 10 | **58** | **4ኛ** |
| **12** | ሸበል | 12 | 15 | 8 | 16 | 10 | 19 | **80** | **3ኛ** |
| **13** | እናርጅ | 14 | 13 | 7 | 4 | 12 | 7 | **57** | **5ኛ** |
| **14** | ጎንቻ | 8 | 6 | 10 | 14 | 7 | 10 | **55** | **7ኛ** |
| **15** | እነ ብሴ | 9 | 10 | 4 | 10 | 14 | 9 | **56** | **6ኛ** |
| **16** | ሁለትእጁ | 7 | 10 | 9 | 13 | 6 | 5 | **50** | **10ኛ** |
| **17** | ደ/ማ | 4 | 5 | 4 | 10 | 9 | 3 | **35** | **14ኛ** |
| **18** | ብቸና | 2 | 4 | 1 | 1 | 5 | 1 | **14** | **19ኛ** |
| **19** | ደጀን ከተማ | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | **3** | **20ኛ** |
| **20** | ሞጣ | 4 | 1 | 4 | 0 | 2 | 4 | **15** | **18ኛ** |
| | **ድምር** | **160** | **144** | **147** | **145** | **165** | **153** | **914** | |

**ሰንጠረዥ 1፡ በምስ/ጎ ዞን የስድስት አመት የሰውግድያ ድርጊት በቁጥር (ምንጭ የምስራቅ ጎጃምዞን ፖሊስ መምሪያ)**

ከሰንጠረዡ በግልፅ እንደሚታየው ከ2006 እስከ 2008 ዓ.ም ባሉት ሶስት አመታት የሰውግድያ በሚያበረታታ መልኩ ቀንሶ የነበረ መሆኑን ነው፡ ነገር ግን ቀጥሎ ባሉት ሁለት አመታት ማለትም በ2009 እና 2010 ዓ.ም ቁጥሩ ከሰንጠረዡ ቀድሞ ከተማለከተው አማካይ ከፍ እያለ መምጣቱን መታዘብ ይቻላል፡፡


የስድስት አመቱ መረጃ የሚያሳየው ጎዛምን 85 የሰው ግድያ በማስተናገድ ግንባር ቀደም መሆኑንና ችግሩ በወረዳው እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ነው፡ ከጎዛምን በማይተናነስ መልኩ በባሶሊበን ወረዳ 84 እንዲሁም በሸበል 80 ግድያዎች ተፈፅመዋል፡፡ የእነዚህን ሶስት ወረዳዎች መረጃ በአራተኛነት ከተቀመጠው እነማይ ወረዳ ጋር ስናነፃፅር ጉልህ ልዩነት ማየት ይቻላል፡፡ በእነማይ ወረዳ ባለፉት ስድስት አመታት 58 የሰውግድያዎች የተፈፀሙሲሆን በሶስተኛ ደረጃ ካለው የሸበል ወረዳ በ22 ግድያ ያነሰ ነው፡ ይህም ጎዛምን፣ ባሶሊበን እና ሸበል ወረዳዎች በተለየ ሁኔታ ለችግሩ ተጋላጭና የተለየ ትኩረት እንደሚያስፈልጋቸው ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ በስድስት አመታት ውስጥ ዝቅተኛ የሰውግድያ ያስተናገዱት ወረዳዎች ቢቡኝና ስናን ሲሆኑ እያንዳንዳቸው 28 የሰው ግድያ ብቻ አስተናግደዋል፡፡

በሌላ በኩል የአራቱ ከተማ ማስተዳድሮች ሚጃ የሚያማላክተው የሰውግድያ በደብረ ማርቆስ እጅግ የከፋ መሆኑን ነው፡፡ በከተማው ባለፉት ስድስት አመታት 35 ግድያዎች ሲፈፀሙ ይህም ቢቡኝ (28)፣ ስናን (28) እና አነደድ (32) ወረዳዎች እያንዳንዳቸው ካስተናገዱት ግድያ የበለጠ ነው፡፡ በተቃራኒው በደጀን ከተማ ባለፉት ስድስት አመታት የተከሰቱት የሰውግድያዎች 3 ብቻ ናቸው፡፡

## 2. በምስራቅ ጎጃም ዞን የሰውግድያ ወንጀል ማለጫዎች


### 2.1. ዋነኛ የግድያ መሳሪያዎች

የሰውግድያ ድርጊቶች በተለያየ መሳሪያ የሚፈፀሙ ሲሆን የጥናታችን አካል በነበሩት አምስት ወረዳዎች ከተሚሙ መዝገቦች እና ከቡድን ተኮር ውይይት ሚዳት እንደተቻለው የመሳሪያዎቹ አይነት ላይ ገደብ እንደሌለና በሁሉም አይነት መሳሪያ እየተፈፀመ መሆኑን ለሚዳት ተችሏል፡፡ ከነዚህ ምውስጥ የጦር መሳሪያ እና ሽሜል ዋንኞቹ ናቸው፡፡




***ፓይ ቻርት 1፡ የግድያ መሳሪያዎች***

ከላይ ካለው ፓይ ቻርት ሚረዳት እንደሚቻለው ከተሚሩ 100 የግድያ ወንጀል ማዝገቦች ውስጥ ግማሽ የሚጠጉት ግድያዎች የተፈፀሙት በሽሜል ወይም በዱላ መሆኑን ነው፡ በሽሜል የሚፈፀም ድብደባ የሰው ህይወትን እንዲቀጥፍ ትልቁን አስተዋፅኦ እያደረገ ያለው ደግሞ በአካባቢው አጠራር ጅንፍ በማል የሚታወቀው በሽሜል ጫፍ ላይ የሚጠለቀው የብረት ማጠናከሪያ ነው፡ ለወንጀል አፈፃፀም ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ያለው ጅንፍ ላይ ህጋዊ ክልከላ ተጥሎ ቁጥጥር እየተደረገ ባይሆንም አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ጅንፍ ያለው ሽሜል ይዞ ከገጠር ወደ ከተማ እንዳይገቡ የሚደረግባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ ማንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይም የገበያ ቀናት ላይ ከማጠጥ ጋር ተዳብሎ ለሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት እየሆነ ስለሆነ በሜል የተጀሙ የቁጥጥር ስራዎች እንዳሉ ለሚዳት ተችሏል፡፡




**ፓይ ቻርት 2፡ የሽሜሉ አይነት**

ከፓይ ቻርት 2 እንደምንረዳው በሽሜል ከተፈፀሙት 49 የሰው ግድያ ወንጀሎች ውስጥ ውስጥ 43 በመቶ የሚጠጉት የተፈፀሙት ጅንፎ ባለው ሽሜል መሆኑን ነው፡ ሚረጃው በሚሰበሰብበት ወቅት ግድያው የተፈፀመው ጅንፎ ባለው ሽሜል መሆኑ በግልፅ ከተሜለከተ ብቻ በዚህ ማለጫስር የማዝገብንው ሲሆን ሽሜል መሆኑ ብቻ ተገልፆ ነገር ግን ልዩ ማለጫካልተቀማጠለት ጅንፎ የሌለው ሽሜል በሜል ወስደነዋል፡፡ በመሆኑም ጅንፎ በሌለው ሽሜል ተፈፅሜል በሜል ከተማዝገበው 15 የሰው ግድያ ወንጀሎች ውስጥም ጅንፎ ባለው ሽሜል የተፈፀሙ ግድያዎች ሊኖሩ

የሚችሉበት እድል አለ፡፡ ይህ ከግምት ውስጥ ሲገባ በዞኑ በሽሜል ከሚፈፀሙየሰው ግድያ ወንጀሎች ውስጥበጅንፎ ሽሜል የሚፈፀሙየአንበሳውን ድርሻ እንደሚይዝ መደምደምይቻላል፡ ፡

በሌላ በኩል ሽጉጥና ጠመንጃ ከሽሜል በመቀጠል ዋንኛ የግድያ ማሪያ ናቸው ፡ የጦር ማሪያ ማያዝ በዞናችን ልክ እንደክብር ማለጫተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን ያለእድሜገደብ ከልጅነት ጀምሮ ማሪያ ማያዝ ይዘወተራል፡፡ የእከሌ ልጅ ማሪያ አለውማል እንደጀብድ እና ዝና ሆኖ ይቆጠራል፡፡ ይህምበማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነትን ለማትረፍ ብሎምእንደሴት ማበያ እና ማስፈራሪያምይቆጠራል፡፡

ከግድያ ወንጀል ጋር በተያያዘ በተለይምየግድያው ማስኤ በቀል ሲሆን ተገዳዩ ዝግጁ ሆኖ ይጠብቃል ተብሎ ስለሚታ ሰት ገዳዩ ከሽሜል ይልቅ የጦር ማሪያ የሚጠቀምበት እድል ሰፊ ነው ፡ ይህምበማያዳግምሁኔታ ነፍስን ለማጥፋት ካለ ከፍ ያለ ቅድመዝግጅት እና የመግደል ሀሳብ ጋር ይያያዛል፡፡ በሽሜል የሚፈፀም ድብደባ በመጀመሪያ መግደልን አላማ አድርጎ ላይፈፀም የሚችል ሲሆን ወድያው ሞትን ባያስከትልም እየዋለ እያደረ እንዲሁም ተደብዳቢው እየታከመ እያለ ለእልፈተ ህይወት የሚበቃበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው ጥቃት ፈፃሚው ከያዘው አላማ አንፃር የግድያ ማሪያውም ሊለያይ እንደሚችል ነው ፡ በሚሆኑም በጦር ማሪያ ተጠቅሞ ጥቃት ያደረሰ ግለሰብ የመግደል አላማውን በበለጠ ግልፅ አድርጎ ያሳያል ማለት ይቻላል፡፡

የማሪያውን ህጋዊነት በተማለከተ ግድያ የሚፈፀሙ አልፎ አልፎ በህጋዊ መሣሪያ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ ግድያ የሚፈፀምባቸውመሣሪያዎች ህገወጥሆነ ውይገኛሉ፡፡

| የማሪያውህጋዊነት | በቁጥር |
|---|---|
| **ህጋዊ/የተማዘገበ** | 7 |
| **ህገወጥ** | 13 |
| **የሚሊሽያ/ፖሊስ** | 3 |

### ሰንጠረዥ2፡ የጦር ማሪያውህጋዊነት


በተደረገው የማዛግብት ምርመራ ማስረት በጦር ማሪያ በተፈፀሙት 23 የግድያ ወንጀሎች ስለማሪያው ህጋዊነት ከላይ ካለው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህም ከ23ቱ የግድያ ወንጀሎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ህገወጥ በሆነ ማሪያ የተፈፀሙነበሩ፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ከመደረሱ በፊት በተለይም በህገ ወጥ ማሪያ ግድያውን የፈፀሙግለሰቦች በተደራራቢ

ወንጀል የሚከሰሱ መሆኑን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ህገወጥ ማሪያዎችን እየተሰሩ ያሉ የተለያዩ የቁጥጥር ስራዎች ቢኖሩም የህገወጥ የማሪያ ዝውውርን በተደራጀ ሜኩ እና በህግ ማዕቀፍ በታገዘ ሁኔታ ከመቆጣጠር አንፃር ከፍተኛ ክፍተት አለ፡፡ መንግስት ጣልቃ ገብቶ ከእንደዚያ አይነት ድርጊት እንዲቆጠብ እና ማሪያ የሚይዘውም ሰው ራሱን ያወቀ መሆኑን ሚረጋገጥ አለበት፡፡ ህጉ የፀጥታ አካላት ቅድመመከላከል እንደያደርጉ ማ ቆ ሆኗል ተብሎ ይተቻል፡፡ ሰንጠረዡ እንደሚያማለክተው በግለሰብ ማሪያዎች ከሚፈፀሙወንጀሎች ባሻገር በመንግስት ማሪያ የሚፈፀሙየግድያ ወንጀሎችምትኩረት እንደሚሹ ያሳያል፡፡ ፖሊስና ሚሊሻዎች በአደራ የሚሰጣቸውን የጦር ማሪያ በሌሎች በማ ጠቅ ወይም አሳልፎ በማስጠት ከሚከሰተው የግድያ ወንጀል በተጨሚ ራሳቸውበወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑበትና የነፍስ ማጥፋት የሚያደርሱበትም አጋጣሚአለ፡፡

ከላይ እንደቀረበው በማሪያ እና በሽሜ የሚፈፀሙግድያዎች የተለመዱና መደበኛ የግድያ መንገዶች ሲሆን አልፎ አልፎ አሰቃቂና ለየት ያሉ የግድያ አይነቶችምይስተዋላሉ፡፡ ለምሳሌ በ2005 እና 2006 በተለይ በደጋሜው ሁለት እጁ እነሴ አካባቢ በመጥረቢያ ወይም በፋስ ከትክቶ መግደል ይስተዋል ነበር፡፡ በሌላ በኩል ወንጀሉ የተፈፀመው በደም ፍላት ወይም ጊዜአዊ ጠብ በሚያንበት ጊዜ ገዳዩ በአካባቢውባገኘውነገር ድርጊቱን ሲፈፅም ይስተዋላል ለምሳሌ ቢላ፣ ድንጋይ ወይምመቀርቀሪያን ማንሳት ይቻላል፡፡

### 3. በምስራቅ ጎጃምዞን የሰውግድያ ምክንያቶች

በምስራቅ ጎጃም ዞን የሰው ግድያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምርና አሁን ባለንበት ዘመን ሁሉ አሳሳቢ ሁኖ እንዲቀጥልና እንዲፈፀም ያደረጉ የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሉ በቡድን ተኮር ዉይይትና ለናሙና ከተወሰዱና ከታዩት ማዛግብቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ምክንያቶችም ለሰው ግድያ በዞኑ እንዲፈፀም በጣም በከፍተኛ ደረጃ አስተዋፅኦ እያደረጉ ያሉትንና ዝቅተኛ አስተዋፅኦ እያደረጉ ያሉትን ምክንያቶችን ከናሙና ከተወሰዱ ማዛግብቶችና በቡድን ተኮር ዉይይቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡




**ግራፍ 2፡ የ ግድያ ማ ስ ኤዎች**

### 3.1. በድንገ ተኛ እና እለታዊ ግጭት (ደምፍላት)

ከላይ ከተቀማጠው ግራፍ እንደምን ረዳዉ ለሰዉ ግድያ ወንጀል ምክንያት ከሆኑት ዉስጥ የአንበሳዉን ድረሻ የሚዙት ደም ፍላትና ቂም በቀል ናቸዉ፡፡ ለግድያ ምክንያት የሆኑትን ለማየት ለናሙና ተሞ ጠዉ ከታዩት 100 ማዛግብት ዉስጥ 31 የሚሆኑት የግድያ ወንጀሎች የተፈፀሙበት ምክንያት በድንገ ተኛ እና እለታዊ ግጭት በተፈጠሩ ፀቦች ነዉ፡፡ ይህ ማለት በዝሆኑ ለግድያ ማ ስኤ ከሆኑት ነገሮች 31 ፐርሰንት የሚሸፍነዉ በድንገ ተኛ እና እለታዊ ግጭት ምክንያት የሚፈጠሩ ናቸዉ፡፡ ሰወች ነገሮችን ታግሰዉ ማለፍ ሲችሉ በትንሽና በቀላል ነገር በተለይም ደግሞ ማጠጥ ከወሰዱ ስሜታዊ በመሆን ሰዉን በማጥቃት ለግድያ ምክንያት እየሆኑ ነዉ፡፡ ሰወች ተራ እና ቀላል በሆነ ነገር ስሜታዊ በመሆን የሚያማጠዉን ተጠያቂነት በሰከነ መንፈስ ማሰብ ባለመቻል ምክንያት ለሰዉ ህይወት መጥፋት ምክንያት እየሆኑ ይገኛሉ፡፡ በደም ፍላት የሚፈጠሩ የህይወት መጥፋት ገዳይ ሆን ብሎ ለመግደል አቅዶበት ወይም የሆነ ጥቅም ለማግኘት ብሎ የሚያደርገዉ ሲሆን ተጎጅ ከተጠቃ በሁዋላ ወዲያዉኑ ወይም በህክምና እርዳታ ላይ እያለ ህይወቱ ሊያልፍ ይችላል፡፡ በናሙና ከታዩት ማዛግብቶች ማካከል ለሰዉ ግድያ ከፊት ለፊት የሚታየዉ ምክንያት ደምፍላትና ቂምበቀል ይሁን እንጅ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ቡድን ተኮር ዉይይትና ከታራሚዎች ጋር በተደረገ ቃለ ማጠይቅ ለግድያ

ወንጀል ትልቁ ምክንያት ሜት መሆኑን እና በሜት የተነሳ ግጭት ደምፍላትን አምጥቶ ወይም ቂምአስይዞ ለሰውግድያ እያበቃ መሆኑን ለማ ንዘብ ተችሏል፡ ፡

## 3.2. ቂምበቀል

ከላይ በሰንጠረዡ እንደምንማለከተዉልክ እንደ ደምፍላት ሁሉ ቂምበቀል ሌላኛዉለሰዉልጅ ግድያ ወንጀል እንደዋና መንስዔ ሆኖ ይገኛል፡ ፡ ይህምማለት ቂምበቀልና ደምፍላት ለሰዉ ግድያ ምክንያት ሆነ ዉ ከተዘረዘሩት ዉስጥ የመጀመሪያዉን ደረጃ ይሸፍናሉ፡ ፡ ቂምበቀልና ደምፍላት በጋራ ሆነ ዉ ከተዘረዘሩትና ከመዛግብት ከተለዩት ወደ 13 ምክንቶች ዉስጥ ከ60 ፐርሰንት በላይ የሚሆነ ዉን ይሸፍናሉ፡ ፡ ለጥናቱ ናሙና ከተመረጡት 100 የሰዉ ግድያ መዝገቦች ዉስጥ 31 መዝገቦች ለግድያዉ መፈጠር ምክንያት ቂምበቀል መሆኑን ያስረዳሉ፡ ፡ በመዛግብት ምርመራ ከተለዩ ምክንያቶች በተጨማሪ በቡድን ተኮርና ዉይይትና በቃለ ማጠይቅ በተገኙ መረጃወች ቂምበቀል በዞኑ ለሰዉግድያ ወንጀል ማስፋፋት ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ መሆኑ ተገልፃል፡ ፡

በምስራቅ ጎጃምዞን ቤተሰቡ በሰዉእጅ የተገደለበተት ለአቅመአዳምየደረሰ ወንድ ካለ ከቻለ ገዳዩን ካልሆነ ደግሞ የገዳዩን የቅርብ ሰዉ የመግደል ባህላዊ ግዴታ አለበት፡ ፡ ደሙን ሳይመልስ አንድ ሰውሰርግ ላይ ወይምየሆነ ጉዳይ ላይ ቁሞአይፎክርምወይምአያቅራራም፡ ከዚህ በተጨማሪም በዝሆኑ ደም መመለስ እንደባህል በመቆጠሩና ደም ሳይመልሱ መቅረት ጥቃትና በተለያየ መልኩ ስለሚያሰድብ ትልቅ ለሰዉግድያ ምክንያት ሊሆን ችሏል፡ ፡ *“ወንድሙ በሰዉ ተገድሎበት ድግስ ተጠርቶ ወደድግሱ ከጓደኞቹ ጋር ሂዶ የታደመወጣት ምግብ ቀርቦለት ማገያ (ወጥ) አድርጉልኝ ብሎ ቢጠይቅ አዉጥተህ አትበላም በማለት በአሽሙር ስለተሰደበ ወድያዉኑ የወድሙን ገዳይ ቤተሰብ የሆነ ን ሰዉ ለመግደል ተገድዷል፡ ፡”* የደም መመለስ አስከፊ ገፅታዉ ደግሞ ብዙ ጊዜ ገዳይ ስለሚጠፋ በደም መመለስ ስርአት ተጠቂ የሚሆነ ዉና የሚገደለዉደካማበመሆኑ ቤት የተገኘ የገዳይ የቅርብሰዉመሆኑ ነ ዉ፡ ይህምበሁሉምጥናቱ በተሰራባቸዉ ወረዳወች የሚታገበር ለሰዉ ልጅ ግድያ ምክንያት የሆነ መጥፎ ባህል ሆኖ አግኝተነ ዋል፡ ፡ ደምመመለስ ብዙ ጊዜ የሚከሰተዉዝምድና በሌላቸዉሰወች መሀከል ነ ዉ፡

## 3.3. የሜት ግጭት

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተገለፀዉ ከጊዜ ወደ ጊዜ በምስራቅ ጎጃምዝሆን ለሰዉግድያ ወንጀል ማስፋፋት የሜት ግጭትየራሱ ድረሻ አለዉ፡ ለናሙና ከታዩት 100 ጥፋተኛ ተብለዉ ዉሳኔ ካገኙት ከባድ የግድያ ወንጀል መዝገቦች ዉስጥ 8ቱ የወንጀል መዝገቦች ለወንጀሉ ማካሰት ቀጥተኛ ምክንያታቸዉሜት መሆኑን ያስረዳሉ፡ ፡ ይህምማለት ከተዘረዘሩት ወደ 13 ከሚደርሱ ምክንቶች ዉስጥ ከ100 ፐርሰንት 8 ፐርሰንቱን በመሸፈን በሶስተኛ ደረጃ ሜት ተቀምጧል፡ ፡

ይሁን እንጅ ከታራሚዎች ጋር በተደረገ ቃለ ማጠይቅና በቡድን ተኮር ዉይይት የተገኘዉ ሚረጃ ለብዙ ሰዉ ግድያ ወንጀል ምክንያት ሜሬት ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡ በሜሬት ጉዳይ የተነሳ ግጭት ደም ፍላትን አምጥቶ ወይም ቂም አስይዞ ለሰው ግድያ እያበቃ ይገኛል፡፡ ለናሙና ከተወሰዱ ሚዛግብቶች (በማጠናዊ) የተገኘዉ ሚረጃና እና በቡድን ተኮር ዉይይትና በቃለ ማጠይቅ (ዓይነ ታዊ) የተገኘዉ ሚረጃ በዚህ ሜልኩ ተጣጥሚዉ ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በአምስቱም ወረዳዎች በተካሄደ የቡድን ተኮር ዉይይትና በሶስቱም ሚረሚያ ቤቶች (በደብረ ሚርቆስ፣ ሞጣ እና ብቸና) ከታራሚዎች ጋር በተደረገ ቃለ-ማጠይቅ በአካባቢዉ ለሰዉ ግድያ ዋና ሜንስኤ ሜሬት ሚሆኑን ሁሉምተስማምተዉበታል፡፡

ሜሬት በምስራቅ ጎጃምዞን ለሰዉ ግድያ ትልቅ ምክንያት የሆነበት ብዙ ምክንቶች እንዳሉት በጥናቱ ላይ በቡድን ተኮር ዉይይት የተሳተፉ አካላት በሰፊዉ አብራርተዋል፡፡ ከሁሉምበላይ ለአካባቢዉ ማህበረሰብ ሜሬት ትልቁ ሃብት ብቻ ሳይሆን የሀብቶችምሁሉ ምንጭነ ው፡ በዞኑ በጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ ሜኖር የሚቻለዉ በከተማምሆነ በገጠር ሜሬት ካለዉነ ው፡ በዚህም ምክንያት የሀብቶች ሁሉ የበላይ የሆነ ዉንና የሀብቶች ምንጭየሆነ ዉን ሜሬት ለማግኘት ህብረተሰቡ የማይሞክረዉነገር የለም፡ ለዚህምህጋዊ በሆነ ምሆነ ህጋዊ ባልሆነ (ወንጀል ሚፈጸምን ጨምሮ) ሜንገድ ሜሬት ለማግኘት ይሞክራል፡፡ ሌላዉ ፍትሀዊ የሆነ የሜሬት ስርጭት አለሜኖሩ ሜሬት ለሰዉ ግድያ ወንጀል ሜንስኤ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ሃብት ያላቸውና አቅም ያላቸውሰዎች በተለያየ ሜንገድ (በማካራየትና በእዳ ሰበብ) ብዙ ሜሬት ይዘዉየሚጠቀሙስላሉ ሜሬቱ የተወሰደበት በህግ አግባብ ተከራክሬ የማስሚለስ እድል የለኝም ብሎ በማሰብ ገድሎ ወይምበዛቻ ሜሬቱን ለማስሚለስ ይሞክራል፡፡

ከምንምበላይ ግን ሜሬት እንዲህ ለግድያ ምክንያት የሆነበት ምክንያት ተብሎበሁሉምየቡድን ተኮር ዉይይት በተለይም ከፍትህ አካላትና ከገጠር ሜሬት አጠቃቀም ባለሚያ የተወከሉት በአፅንኦት የገለፁት የክልሉ የገጠር ሜሬት አዋጅ የነበረበት ክፍተት ነዉ፡ የክልሉ የሜሬት አስተዳደር አዋጅ 133/98 ዋና ክፍትት የነበረዉ ዉርስን በተማለከተና የወራሽነት ደረጃዎች ላይ ነበር፡፡ ወራሾችን በአራት ደረጃዎች በማስቀሜጥ የሜጀሚሪያ ደረጃ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ እስከ 18 ዓሜት ያሉት ህፃናት፤ በሁለተኛ ደረጃ የሜጀሚሪያ ደረጃ ወራሽ ከሌሉ ከ18 ዓሜት በላይ ሆኖ ሜሬት የሌለዉ፤ በሶስተኛ ደረጃ ከ18 አሜት በላይ ሆነ ዉ ሜሬት ያላቸዉ እና የሜጨረሻ ደረጃ ወራሽ የሚቹ እናትና አባት በማለት ያስቀምጥነበር፡፡ ችግሩ ይፈጠር የነበረው የሜጀሚሪያ ደረጃ ወራሽ ህፃን (እስከ 18 ዓሜት እድሜ) ካለ ነው፡ ሚቹ ለምሳሌ 12 ገሜድ ሜሬት ካለዉ ሁሉንምበህጉ ማሰረት የሚወርሰዉ ህፃኑ ነ ዉምንምእንኳ ከ18

አመት በላይ የሆኑና መሬት የሌላቸዉ ወንድሞችና እህቶች ቢኖሩትም፡ ይህን ኢ-ፍተሃዊ የሆነ ን የመሬት ዉርስ ለማካላከልና መሬት ለማግኘት እድሜያቸዉከ18 በላይ የሆኑት በተለይም ምንም መሬት የሌላቸዉ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ወራሽ የሆነ ዉን ህፃን ለመግደል ይዳዳሉ፡፡ በቅርቡ ተሻሽሎ የወጣው የሜሬት አዋጅ ቁጥር 252/2009 በዉርስ ምክንያት የሚመጣዉን ኢ-ፍትሃዊ የሆነ የዉርስ ሂደት በማስተካከሉና ሁሉም የሟች ልጆች ባላቸዉ ደረጃ ኢንዲካፈሉ በማድረጉ በዚህ ምክንያት የሚፈጠረዉን ግጭት ሊቀንስዉእንደሚችል ይጠበቃል፡፡

ሌላውከላይ ከተገለጸዉጋር በተመሳሳይ መልኩየነበረዉየአዋጅቁጥር 133/98 የክልሉ የመሬት አዋጅ ክፍተት የቤተሰብ አባል በሚል ለወራሽነት የሚያበቃበት ስርአት ነዉ፡ የእናት አባቱን መሬት በተዘዋዋሪ ለመዉረስ የፈለገ ሚያደርገዉየነበረዉየወለደዉን ልጁን እናት አባቱ ቤት ላይ በማስቀመጥ የቤተሰብ አባል በሚል ለዉረስ እንዲበቃ ማድረግ ነበር፡፡ የልጅ ልጅ ሆኖ ሟች ቤት የገባዉበተለይም ህፃን ከሆነ የሟች ልጅ የሆነ ከ18 አመት በላይ የሆነ ና ምንም መሬት የሌለዉቢሆንምመሬት በዉርስ ማት ለማት የሚስጠዉበህጉ ማስረት ለህፃን የልጅ ልጅ ስለሆነ ዋና ልጅ ይህን ህፃን ለመግደል ይሞክር ነበር፡፡

ከወረዳ እስከ ቀበሌ የሚገኙ የመሬት አስተዳደር ባለሚያዎች ብቁና የሰለጡኑ እንዲሁም ከብልሹአሰራር የጸዱ አለመሆናቸዉችግሩ እንዲባባስ አድረጓል፡፡ የገጠር መሬትን የሚመሩት ብዙ ጊዜ በመሬት አስተዳደር የሰለጡኑ ባለሚያዎች ሳይሆኑ ከተለያየ ሴክተር ማስሪያ ቤት እየተዉጣጣየሚመጡባለሚያዎች ናቸው፡ ሚያዉን የሚመሩት በመሬት አስተዳደር ወይምሚያውን ይመጥናል ተብሎየሚታሰብ በማስኩየሰለጡኑ ሳይሆኑ በማማህርነት የቆዩ፣ በማንኛዉምየህግ ሚያ የሰለጡኑ፣ ጂኦግራፊ ያጠኑ ወይም ግብርና የተማሩ ግለሰቦች ናቸው፡ይህም ህጉን በትክክል በመተግበርና ፍትሀዊነት በማስፈን በኩል ችግር ስለሚፈጥር ህብረተሰቡ የግሉን መፍትሄ እንዲፈልግ ይገፋፋዋል፡፡

መሬት በ1989 ሲደለደልምቢሆን ሳይንሳዊ በሆነ ና በተሟሏ የሰዉሃይል የተሰራ አልነበረም፡ ድልደላዉየተሰራዉከገበሬ ኮሚቴ ተዋቅሮ ሳይንሳዊ ባልሆነ መንድና ትክክለኛ ሚረጃ ሳይያዝ መሆኑ ችግር ፈጥሯል፡፡ የተማዝገበ ሚረጃ ባለሞሩም ምክንያትና ድልደላዉ ፍትሀዊነት የጎደለዉነዉተብሎየክልሉ መንግስት ስላማ በትምየመሬት ባለይዞታነት ሚረጋገጫደብተር ለማስራት ያመቸ ዘንድ ትችታ የሚባል ስርአት ተዘርግቷል፡፡ በማስተቸት ለትክክለኛው ባለይዞታ ለሆነ ግለሰብየመሬት ባለይዞታነት ሚረጋገጫደብተር ለማስራት በሚሞከርበት ጊዜ በትችታመሬት የተነ ጠቀ ካለ ወደ ግድያና ፀብየሚያመራበት ሁኔታ ይታያል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በማስየ ላይ ውሃ ለቀቀክብኝ፣ ግጦሼን አበላህብኝ፣ ሜሬት ገፋህብኝ፣ የወል ሜሬትን ገፍተህ አረስህ በሚሉ ሜሬት ነክ ሰበቦች ወደ ግጭት በመግባት ለግድያ ሲያደርሱ ይስተዋላል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተገለፁት ዋና ዋና ምክንያቶችና ሜሬት ለሰዉ ግድያ ወንጀል በዞኑ ዉስጥ ሚፈፀምቀዳሚምክንያት ሚሆኑን የቡድን ተኮር ዉይይት ተሳታፊዎች ጋር በተደረገ ቃለመጠይቅ ለማ ንዘብ ተችሏል፡፡

### 3.4. በፍትህ አሰጣጥ ባለሚ ካት ወይምበሀሰት ሚሥሰር

በፍርድቤት የፍትህ አሰጣጥ ስርአት ሁሉምነ ገር ዉሰኔ የሚሰጠዉማስረጃን ማሰረት በማድረግ ሚሆኑ እሙ ነ ዉ፡ ከማስረጃዎችምመካከል የአይን ምስክር ዋና ማስረጃ በሚሆን ያለግላል፡ ፡ ለዚህምነ ዉ ምስክርች የፍርድቤቶች አይንና ጆሮ ናቸዉየ ሚባለዉ፡ ይሁን እንጅ ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በምስራቅ ጎጃም ዞን የአይን ምስክሮች እዉነ ትን ከሚናገር ይልቅ በሀሰት በሚመስከር የሚፈልጉትን ለሚጥቀምና የማይፈልጉትን ለሚጐዳት በማሰብ የፍርድቤቶችን ስራ በማበላሸት በፍትህ አሰጣጡላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድረዋል (Mekonnen Nigusie and Aberha Melese, Perjury in East gojjam zone, 2009, debre markos university, p 31)፡፡ በዞኑየሀሰት ምስክርነ ትሰዎች ያለአግባብ እንዲታሰሩና ጥፋተኛ የሆኑትም ያለአግባብ ከተጠያቂነ ት ነፃ እንዲሆኑ እያደረገ ይገኛል፡፡ ይህ ችግር እየሰፋ በሄደ ቁጥር ህብረተሰቡ በፍትህ ላይ ያለዉን አሜ ታ በማሳጣት ፍትህን በራሱ እጅ ለማስጠት ስለሚሻ ለሰዉግድያ ማከሰት ምክንያት ይሆናል፡፡ ምስክሮችበሀሰት ከተደራጁ የፍትህ አካላት በተለይም ዓ/ህግ እና ፍ/ቤት ስህተት እንዲሰሩ ምክንያት ይሆናል፡፡

የአይን ምስክሮች ህግን በሙ ተርጎምበኩል የፍትህ አካላት ላይ ተፅዕኖ ባያደርጉምየፍትህ አካላት በተለያየ ምክንያት ስህተት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ህግን በትክክል ቢተረጉሙምህብረተሰቡ ህጉን አምኖበትና ተቀብሎት የወጣ ካልሆነ ፍትሀዊ አይደለም ብሎ በማሰብ የራሱን እርምጃ እንዲወስድ ሊያደርገ ው ይችላል፡፡ እንደምሳሌ የሚጠቀሰዉ ወንጀል ሰርተዉ ሚረሚያ ቤት ቆይተዉበይቅርታና በምህረት ሲወጡበተለይምተጎ ጅየሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ተገቢነ ዉ ብለዉሰለሚያምኑ ለብቀላ ይገፋፋሉ፡፡

በአጠቃላይ ፍትህ በተለያየ ምክንያት ሲዛባና ተገቢ የሆነ ዉሰኔ አላገኘሁም ብሎ ማህበረሰቡምሆነ የግል ተበዳይሲያምን ፍትህን በእጁ ለማግኘት ወንጀል ይሰራል፡፡ ይህም በምስራቅ ጎጃምዞን ለሰዉግድያ ወንጀል እንደአንድ ምክንያት ይወሰዳል፡፡

## 6. በምስራቅ ጎዛምዞን ለሰውግድያ ወንጀል ምቹና አበረታች ሁኔታዎች

### 7.1. ማጠጥ

በዋናነት ለሰዉ ግድያ ወንጀል ምቹ ሁኔታዎች ተደርገዉ ከሚወሰዱ ነገሮች አንዱ የአልኮል ማጠጥ እንደሆነ ይገለጻል፡፡ በተለይም ወጣቱ በገባያ እና በበአላት ቀናት ከማጠን ባለፈ በማጠጣት ለወንጀል እንደሚጋ ሳሱ ሚረጃዎች ያማላክታሉ፡፡ ማጠጥ በጠጠብት ሰዓት ያለፈ ቂምን በማሰብ ለግድያ ወንጀል ይዳረጋሉ፡፡ ይሄዉም ወጣቶች ከተማ ማሻታ በታ/ማጠጥ ቤት/ ሲጠጡ ካማሹ በኋላ በቡድን ከከተማ ወጥተዉ መንገድ ላይ በማጠበቅ ድብደባ ሊፈጽሙእንደሚችሉ ተጠያቂዎቹ አብራርተዋል፡፡ ይሄንንም በጉዳዩላይ እዉቀቱ ያላቸዉ የፖሊስ አባል እንደሚከተለዉይገልጻሉ

> *ስካር አለ በማጠጥ ተገፋፍቶ ወጣቱ ከማጠን በላይ ጠጥተውበቡድን ይወጣሉ መንገድ ላይ ከከተማው ወጣ እንዳሉ ይደባደባሉ ይጋደላሉ፡፡ በሌላ የንብረት ወይም ግላዊ ጠብ ኖሮ እነ ዚህን ምክንያቶች ያደርጉና ከሰከሩ በኋላ ያንን ሰውየ መጀመሪያ ላይ ተቀያይመው የነበረውን ሰውየ ካገኘውይደበድበዋል፡፡*

ከማጠጥ ጋር ተያይዞም እንደምቹ ሁኔታ የተለያዩ ወቅቶችም ለወንጀል ማብራከት ምክንያት ናቸዉ፡በበጋ ወራት ምርትን ከሸጡበኋላ ከተማዉስጥ ሲጠጡያማሻሉ፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንደገለጹት አርሶ አደሩ ወቅቱን በስራ አሳልፎ በዚህ ሰዓት ለመዝናናትና ለስኬት ማለጫ በማድረግ ማጠጥን በማዘዉተር እና በስካር መንፈስ በማሳሳት የቆየ ቂም/በእርቅ የተወሰነ ግጭትን ሳይቀር/ ምክንያት በማድረግ የተለያዩ ማሳሪያዎችን ሳይቀር በማጠቀም ለከባድ ወንጀል ይዳረጋል፡፡ የሞጣከተማፖሊስ የሆኑትየጥናቱ ተሳታፊ እንደገለጹት፡

> *ሰዎች ሲጠጡበውስጣቸው ይዘውት ወይም አቂመውት ይቆዩና ሞቅ ሲላቸውይኸንን ነገር ይፈፅማሉ*

### 7.2. የሀይማኖት አባቶች ሚና ማነስ

ለወንጀል ማብራከት የባለድርሻ አካላት ሃላፊነትን አለመወጣትም አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ ከነ ዚህምዉስጥየሀይማኖት አባቶች ሚና መቀነስ አንዱነዉ፡ በእርግጥየንስሀ ልጆቻቸውን እየያዙ በየወሩ ቃለ ጉባኤ እየያዙ እየመከሩ እያስተማሩ ችግር ያለበትን ደግሞ እረፍ እያሉ፣ እየመከሩ ሀይማኖትን ቀንተው እያስተማሩ ወንጀል ወይም ግድያ ለመቀነስ የሚሰሩ በርካታ የሀይማኖት አባቶች መኖራቸውአይካድም፡ ነገር ግን ወንጀልን በተለይም ግድያን ከመቀነስ አኳያ የሀይማኖት አባቶች ሚና እየቀነሰ መምጣት እተስተዋለ ነዉ፡ ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶች ማንሳት ይቻላል፡፡ አንደኛዉ በሀይማኖት አባቶች በራሳቸዉ የተፈጠረ ችግር ሲሆን ሌላኛዉበምእመኑ/በንስሃ ልጆቻቸው/በኩል ያለ ችግር ነዉ፡

በዚህ ጥናት ተሳታፊ የነበሩት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና እምነት የሃይማኖት አባቶች እንደገለጹት አንደኛዉ ችግር የሃይማኖት አባቶች ብዙ የንስሃ ልጆችን ማያዝና ሁሉንም በምክር ለማድረስ መቸገር ነዉ፡፡ ግድያ የሚፈጽሙት በብዛት ወጣቶች ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንፃር እነዚህን ወጣቶች ቢያንስ እንኳን ከወር አንድ ቀን ስለወንጀል ሃጢያትነት ተገቢ፣ አለሚሆን ማስተማር አይችሉም፡በተጨማሪም ሀሰት ሲማከር እየታወቀ ሳይቀር እንደንስሃ አባት ከማዉገዝ ወይም ከልጅነት ከማብረር ይልቅ ሰምቶ ዝምማለትወንጀሉ በማህበረሰቡ ውስጥ ቀስ በቀስ ነውርነቱ እንዲጠፋ እያደረገውነዉ፡፡

የሃይማኖት አባቶች በበኩላቸዉየግድያ ወንጀልን ለመቀነስ እንደአባት የበኩላቸዉን እየሰሩ መሆናቸዉን ነገር ግን በርካታ ተግዳሮቶች እንዳሉባቸውይገልጻሉ፡፡

*ካህናት በሀዋርያት የተሰየሙሰዎች ናቸዉና ጊዜያቸውን ማስዕዋት አድርገውሌት ተቀን የሚተጉ ሰዎች አሉ፡፡ እኛ የተጣላዉን ለመገደል የተነሣሣውን ሰውአንድ ቀን ለማሰብሰብ እና ለሚቅ እንጥራለን፡፡ ነገር ግን "አይልቦሙወኢይሬዕዩ እዝልቦሙወኢይሰሙ ይላል ቅዱስ ዳዊት "አይን እያላቸውየማያዩ ጆሮ እያላቸዉየማይሰሙ አሉ፡፡ ስርቆት ከጀማሩ በዚያውየማፋፋቸው ምንምየማይማሰቸውአሉ፡፡(ከአይነታዊ ማጠይቅ)*

በተጨማሪም ሌሎች ተጠያቂዎች የሃይማኖት አባቶች ሚና ማነስ ምክንያት ብለዉየሚጠቅሷቸዉ አሉ፡፡ ይሄዉም አብዛኛዉ ማህበረሰቡ ለሃይማኖት ተገዥነቱ መቀነስና ከሃይማኖት ይልቅ ለባህል ተገዥ መሆኑ ሲሆን ሌላዉ ደግሞ በብልጭልጭ ነገር በጀብደኝነት በመሣሪያ ባለቤትነትን ማታለል እና እነዚህን እንደትልቅ ነገር መቁጠር ብሎምሃይማኖታዊ ክልከላን ትእዛዝን መጣስ መዳፈር ናቸው፡ ስለሆነም የወጣቱ ታዛዥነቱ እና አባት አክባሪነቱ መቀዛቀዝየሃይማኖት አባቶችን ተስፋ እያስቆረጠይገኛል፡፡

ነገር ግንየሀይማኖት አባቶች አሁንምቢሆን ተፅእኖአቸውን ሊያሳድጉ እንደሚችሉና ጠንክረዉ ካስተማሩ፣ ከማሩ ማንም ከእነርሱ ምክር እንደሚይወጣ ተስፋ እንዳላቸው የቡድን ተኮር ውይይቶች ተሳታፊዎች ተስፋቸውን ይገልፃሉ፡፡

*የንስሃ አባቶች የነፍስ አባቴ እንደዚህ አድርገሀል ካሉኝ ሁሉን ነገር ትቼ በእሣቸው ቃል ነውየምገባ፡፡ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ስልጣን ቅድምእንዳሉት አልተጠቀሙበንም እንጅ ቢጠቀሙበን የወንጀል ስርዓቱ ይቀንሣል፡፡ ስንጣላ የዚያምአባት አለውየእኔም አባት አለኝ አብረውቁጭብለውአይተውከአባትነት አወጣሃለሁኝ ይኸን ይኸን እኳ ብለው አንብበውየሜዳ መሆኑን ቢያሰውቁ ማንኛውም ሰውአይንቀሳቀስም፡የሀይማኖት ሚሪ አባቶች እንዲሁምትላልቅ የአገር ሽማግሌዎች የማስታረቅ ቸልተኝነት አለባቸው፡ ሰው*

*በትንሹምበትልቁምይጣላል ይህ ከዘገየ ደግሞወደ ግድያ ይደርሳል ያንን ቶሎየመቅጨት ስራ ከእነሱ ይጠበቃል(የቡድን ተኮር ውይይት)፡፡*

### 7.3. ደካማየ ወንጀል ህግ አፈፃፀም

የሃገሪቱ የወንጀል ህግ አፈጻጸም ክፍተት፣ የማህበረሰቡ ትክክለኛ መረጃ አለማጠትና የሃሰት ምስክርነት በራሱ ለሰዉግድያ ወንጀል ከማህበረሰቡ አለመቀነስ ምክንያት እንደሆነም በዚህ ጥናት ታይቷል፡፡ ይሄም በግድያ ወንጀል በሚያዙ ሰዎች ላይም ተገቢ አስተማሪ እርምጃ አለመውሰድ እንደምክንያት ተነስቷል፡፡ የታሰሩ ሰዎች ከማረሚያ ቤትሲወጡየ ጥቃት ሰለባ እሆናለውየሚል ስጋት ግለሰቦች ስለ ግድያ ወንጀል የሚያውቁትን እንዳይመሰክሩ እያደረጋቸው በመሆኑ የሚወሰዱየ ቅጣት እርምጃዎች ጠንካራ እንዲሆኑ ተሳታፊዎች ጠይቀዋል፡፡

የቅጣቱ ተመጣጣኝ አለመሆን ሰዎች ተደጋጋሚ ወደ ወንጀል እንዲሰማሩ እንደሚያደርግ ተጠቁሟል፡፡ ይሄንንምየ ጥናቱ ተሳታፊዎች እንደሚከተለዉ ይገልፁታል፡፡

*እገሌ ገድሎ ምን ሆነ ደርጅቶ አይደል የማጣውበሚል መሳሳትን ይፈጥራል፡፡ በዛ ላይ በአማክሮ ይፈታል ወይምበሚይታወቅ ምክንያት ይፈታል ይህ በህብረተሰብ ውስጥየሚይገባ ስሜት ይፈጥራል፡፡*

በማረሚያ ቤቶች የሚሰጡትን አገልግሎቶችም እንደ ጥሩ እድል በመቁጠር ከእስር ሲፈታ ስለሚሰራውወንጀል እና በቀል የሚያስብ ይኖራል፡፡

*ሰው እየገደለ ማሽን ሲማር ይውላል፤ ይህ ደግሞ ስራ ያጣ ሰውን ወንጀል ሰርቶ ገድሎ እንዲገባ ሊፈልግ ያደርገዋል፡፡ ማረሚያ ቤት የእውነ ትምመቀጣጫመሆን አለበት፡፡*

ምስክሮች የሚደረግላቸዉ ከለላ ደካማ መሆን፣ በሃሰት የሚመሰክሩ ሰዎችን አጣርቶ ለፍርድ አለማቅረብም ሌላዉ የህግ ክፍተት እና ለሰዉ መግደል ወንጀሉ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ተሳታፊ ፖሊሶች ይገልጻሉ፡፡

*ምስክርች ለነፍሳቸውይሰጋሉ የነፍስ ግድያን ወንጀል ሰውማስረጃ አልሆንምእያለ ነው ማስረጃ እያጣን ነውበዚህ ምክንያት፡፡ ማስረጃ የሚሞት ከሆነ የህግ ከለላ ከሌለውየህግ ጥበቃ ከሌለውለምንድን ነውማስረጃ የምንሆን እያለ ነው፡ በሌላ በኩል ደግሞበሀሰት ተማስክሮበትምገድለሀል ተብሎየሚፈረድበት አለ፡፡ የፍትህ ስርዐቱ እነዚህን የማጥራት አቅምአልገነባም፡ የፍትህ ስርዐቱ ላይ ህብረተሰቡ ያለውእምነት ደካማነው(ቁልፍ አይነ ታዊ ማጠይቅ)፡፡*

### 7.4. ህገወጥየ ጦር መሣሪያ ዝውውር

የሰዉ ግድያ ወንጀል ከሚፈጸምባቸዉ መሳሪያዎች አንዱ የጦር መሳሪያ ነዉ፡፡ ይህ የጦር መሳሪያ በማህበረሰቡ በህጋዊም ሆነ በህገወጥ መንገድ በግለሰቦች እጅ ይገኛል፡፡ ይሄም

በተደጋጋሚ የግድያ ወንጀል ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ማህበረሰቡ የጦር መሳሪያ ባለቤትነትን እንደ ትልቅ የክብር ማለጫ አድርጎ ስለሚቆጠር መሳሪያ የሌላቸዉ ሰዎች ያላቸዉን ሰዎች በመግደል መሳሪያ መቀማትና ወደጫካ ማሽፈት የተለመደ መሆኑን ተሳታፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

የሸበል ወረዳ ቡድን ተኮር ዉይይት ተሳታፊ እንደገለጹት፡

*በአጠቃላይ መሣሪያን እንደባህል የመዉደድ በወረዳችን ላይ ይስተዋላል፡፡ በጣምበርካታ ህጋዊ እና ህጋዊ ያልሆነ ትጥቅ መኖር ለወንጀሉ ማባራከት ምክንያት እየሆነ ነዉ ሰፊ የሆነ የመሣሪያ ዝዉዉር አለ፡፡ ብዛት ያለዉበህጋዊ መንገድምየተመዝገበ መሣሪያ አለ፡፡ በህገ ወጥ መንገድምየሚዘዋወሩ መሣሪያዎች አሉ፡፡ ይህን መሣሪያ በአግባቡ ያለማጠቀም በተለይ በቸልተኝነት ለሚፈጸሙ የሰው ግድያ ወንጀሎች ሰፊውን ቦታ ይይዛል፡፡ ለምሳሌሰርግ ላይ ሲፈክሩ መሣሪያ መተኮስን ማንሳት ይቻላል(ቡድን ተኮር ዉይይት)*፡፡

## 8. በምስራቅ ጎጃምዞን የሰውግድያ ወንጀልን ለመቀነስ ሊረዱ የሚችሉ የመፍትሄ ሀሳቦች

### 8.1. የሚሬት አስተዳደርን ማሻሻል

ሚሬት አስተዳደር ላይ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት በተለያዩ ደረጃዎች የሚገኙ የሚሬት አስተዳደር ፅ/ቤቶች የራሳቸውን ጥናት እያካሄዱ የአቅምግንባታ እና በህጉ ያሉትን ክፍተቶች ለማዘጋት ጥረት እያደረጉ ቢገኝም አሁንም ድረስ ሚሬት ዋንኛው የግጭት ምንጭ ብሎም የሰው መግደል ወንጀል ማሻ ምክንያት መሆኑን ቀጥሏል፡፡

በክልሉ የሚሬት አዋጅ ለሶስተኛ ጊዜ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡ የሚሬት ህግ በየጊዜው ማሻሻል የሚያሳየው ሚሬትን በተማለከተ በየጊዜው አዳዲስ፤ ያልተገመቱና ያልተዳሰሱ ጉዳዮች በፍጥነት እንደሚፈጠሩ እና በማህበረሰብ ውስጥም ችግር እየፈጠሩ እንደነበረ እና የህጎቹ ማሻሻልም እነዛን ክፍተቶች ከመሞላት ጋር እንደሚያያዝ ነው፡ የአንድ ህግ ክፍተቶች በተለየ ጎልተው የሚወጡት ወደ ተግባር በሚገባበት ጊዜ በሚሆኑ ሚሬትን በሚማለከት ምሉዕ የሚባል ህግ ማውጣት አዳጋች ሆኗል፡፡ ለምሳሌ በቅርብ የወጣው አዋጅ ቁጥር 252/2009 ከበፊቶቹ የተሻለ የውርስ ክፍፍልን ፍትሀዊ አድርጓል ቢባልምወደ ትግበራ በሚገባበት ወቅት ባልታሰበ ሁኔታ የቆዩ ጉዳዮችን በመቀስቀስ ለግጭት መንስኤ ከሚሆኑ ባለፈ ፍርድ ቤቶችን በሚሬት ጉዳይ ለሚጨናነቅ ዳርጓቸዋል፡፡ በሚሆኑም የሚማለከታቸው የሚሬት አስተዳደር እና የፍትህ አካላት እንዲህ አይነት ክፍተቶችን እግር በእግር በማከታተል ለሚማለከተው የክልል ህግ አውጪ ምክር ቤት ማሳወቅ እና ችግሩ በአዋጅ ማሻሻያ ወይም በማስፈፀሚያ ደንቦች የሚፈታበትን አማራጭ ማጠየቅ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ህጎች ከወጡ በኋላ ችግር እንዳለባቸው እየታወቀ ለረዥምጊዜ በስራ ላይ መቆየታቸውችግር ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ በተጨማሪ ህጎች ወደ

ትግበራ ከመግባታቸው በፊት አንድምታቸውን ለህብረተሰቡ ግልፅ በሆነ ሁኔታ ማሳወቅ አዲስ የሚቀሰቀሱ አለመግባባቶች ሊቀንስ ይችላል፡፡

ከህግ ክፍተት በተጨማሪ ከቀበሌ ጀምሮ ያሉ የሜሬት አስተዳደር ባለሞያዎችን አቅም ማሳደግ እና ከኪራይ ሰብሳቢነት የሚቆጠቡበትን አሰራር ማዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ በቀበሌ ደረጃ የሚመደቡት የሜሬት አስተዳደር ባለሞያዎች ባብዛኛው የተሻለ የትምህርት ደረጃ ያላቸውና ቸው ቢባልም በክልሉ የሚወጡ ህጎችን በአግባቡ ተርጉሞ ከማስተግበር ጋር በተያያዘ አሁን ምድረስ ክፍተት አለ፡፡ ለዚህም አዳዲስ ህጎች በሚወጡበት ወቅት ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ስር ያሉ ባለሞያዎችን ማዕከል አድርጎ ማሰራት ገባዋል፡፡ ከሜሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚታወየውን ኪራይ ሰብሳቢነትም ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ በየደረጃው ከሚሰጥ ትምህርት ባሻገር ጠንካራ የተጠያቂነት አሰራር ማዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ በህግና በሚርህ የሚሰራ የሜሬት አስተዳደር ባለሞያ ማፍራት ከተቻለ ህብረተሰቡም አግባብ ባልሆነ ውማስሚር ሜዱን ይቀንሳል ወደፊትም እራሱ ኪራይ ሰብሳቢነትን የሚፀየፍ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም አንድ ውሳኔ አላግባብ ባልሆነ ሁኔታ ቢወሰን ምበሚቀጥለው ደረጀ ላይ ሊቀለበስ እንደሚችል ለህብረተሰቡ ግንዛቤ በመፍጠር ታችኛው የሜሬት አስተዳደር አካላት ላይ ሊኖር የሚችልን ኪራይ ሰብሰቢነት ሚድረቅ ይቻላል፡፡

ሌላው የሜሬት አስተዳደርን ስራ በማዳተትና ለተሳሳተ ውሳኔ እንደ አንድ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው በቅጡ ያልተደራጀ የሜሬት ሚረጃ አያያዝ በሚሆኑ የተቀናጀና የተደራጀ ሚረጃ አያያዝ መማስረት የባለቤትነትን ጥያቄ በመፍታት ሊነሱ የሚችሉ የሜሬት ባለቤተነት እንዲሁም የድንበር ግጭቶችን ሊቀንስ ይችላል፡፡

## 8.2. የግጭት አስወጋጅ አደረጃጀቶችን ሚና ማሳደግ

አሁን ባለው አወቃቀር ማስረት በዞናችን በየጐጡ አምስት ግጭት አስወጋጆች ሲኖሩ እንደ ቀበሌ ደግሞ ሶስት የሀገር ሽማግሌዎች አሉ፡፡ እነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች እርቅ ላይ ግጭት አስወጋጅዎችን እየገቡ ይደግፋሉ ብሎም ከግጭት አስወጋጆች አቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ይህም አደረጃጀት በጠቅላላ ተጠሪነቱ ለፖሊስ ነው፡ ከነዚህም መደበኛ አደረጃጀቶች ባለፈ ማህበረሰቡ የሚያጋጥሙትን ማንኛውም ግጭትና የፀጥታ ችግር ባሉት ኢ-መደበኛ የሆኑ ማህበራዊ ግንኙነቶች፣ በእድሮች እና በማህበሮች ለመፍታት ይጥራል፡፡ ይህም የእለት ግጭቶች እንዳይጎለብቱና ወደ ከፋ ደምመፋሰስ እንዳያመሩ ያስችላል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ የግጭት አስወጋጅ ኮሚቴዎች በስፋት በእርቅ ስራ የሚያዙት ሀሳቡ ከገዳይ ወገን ሲቀርብላቸው እንደሆነ ይስተዋላል፡፡ የማታረቅ ሀሳቡ በዋነኝነት ከገዳይ በኩል ሊመጣ ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ታረማዎች በሰላም ለመኖር ካላቸው ፍላጎት አንፃር አልገደልኩም

ብለው ቢያስቡ እነ ኳ ለማታረቅና ለማካስ ዝግጁ ሲሆኑ ለግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች የእርቅ ጥያቄ ያቀርባሉ፡፡ ነገር ግን ግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች ይህን ከገዳይ ወገን የሚመጣን ጥያቄ ማጠበቅ የለባቸውም፡ በተለይ በጊዜአዊ ጡብ የሚፈጠር ግድያ በቶሎ እርቅ ካልወረደ ወደ ደም መመላለስ ያደርሳልና ግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች ሁኔታዎችን እየተከታተሉ እግር በእግር እርቅ ማስፈፀምና የእርስ-በእርስ ማጋደሉችን ማካላከል ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል የካሳው ማጠን ላይ ታራቂዎች ሳይስማሙ በመቅረት እርቁ እንዳይሰናከል ሽማግሌዎች ግፊት ማድረግና ከያንዳንዱ ወገን የሞቱትን ታሳቢ በማድረግ ማስፈፀምአለባቸው ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ከሁለቱ ቤተሰቦች ሰውየሞተ እንደሆነ የኔ የበለጠ ሞቷል የሚል ክርክር ጉሜታ አልከፍልምበሚል ለእርቅ መደናቀፍ እንደምክንያት ስለሚቀርብ ነው፡ አንዳንድ ጊዜም አንድ እኩል ወይም ሁለት እኩል ካልሆንን አንታረቀም የሚል እምቢተኝነት ይስተዋላል፡፡ በተጨማሪ ከሁለቱም ወገን ሰው የሞተ እንደሆነ እና አጥፊዎች የታሰሩ እንደሆነ የቅጣት ማጠናቸውን በማፃፀር ጉሜታ ማጠየቅ ይስተዋላል፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ወቅት ሽማግሌዎች የእርቁ አላማ ከገንዘብ ጥቅም ባለፈ ዘላቂ ሰላም እና የተረጋገ ኑሮ መሆኑን በጥልቀት ማስገንዘብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከሟቹ ቤተሰብ በኩል ለእርቅ ትልቅ እንቅፋት እየሆነ ያለው ደም ሚሰው ከሚመጣባቸው እስር በላይ ክብራቸው ስለሚያስጨንቃቸው ለእርቅ ፍቃደኛ አለሚሆን ነው፡ ሌላው በእርቅ ሂደት ላይ እንቅፋት እየፈጠረ ያለው እዳሪ የወጡልጆች ለማግስት እጃቸውን ካልሰጡ አንታረቅም ማለት ነው፡ በዚህ ሁኔታ የህግ አካላት ተጠርጣሪዎችን በህግ ከለላ ስር ያለማስገባት ድክመት የሟቹ ቤተሰብ ማታረቅ እየፈለገ እርቁ ሁሉን አካታች ባለሚሆኑ እንዲያፈገፍግ ያስገድደዋል፡፡ በሚሆኑም የሚመለከታቸው የህግ አካላት በሰው ግድያ ተጠርጣሪዎችን ከተሰደዱበት ይዞ ለህግ በማቅረብ ዘንድ ያላቸውን አቅም በማጎልበት በሟቹና ገዳ ቤተሰብ ማካከል ያለውን የእርቅ ሂደት መደገፍ ይቻላሉ፡፡ በተጨማሪ ምያፈነገጡ ወጣቶችን ወደ እርቅ እንዲገቡ በማድረግ ረገድ የሀይማኖት አባቶች ጣልቃ ቢገቡበት እርቁን አካታች በማድረግ የደምመመላለስን ስጋቻ መቀነስ ይቻላል፡፡

ግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች ከስራ ሰዐታቸው ላይ ቀንሰው የሰው ህይወትን ለማትረፍ እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ሰላምን ለማስፈን ለሚያደርጉት አስተዋፅኦ ምንምአይነት ድጎማ ወይም ደመወዝ ስለሌላቸው አንዳንዴ ስራቸውን ችል እንዲሉ ሆነዋል የሚል ቅሬታ ይነሳል፡፡ በእርግጥ የማስታረቅ ስራ ከሚወስደው ረጅም ጊዜና እልህ አስጨራሽ የማግባባት ስራ አንፃር ብሎም ግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች ግጭት ከተፈጠረ በኋላ ጣልቃ ከመግባት ባለፈ ግጭትን በማካላከል አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ሊያበረታታ የሚችል ጥቅማጥቅም በመንግስት መዋቅር ስር

ተካቶ በተለያየ መንገድ ቢተገበር የግጭት አስወጋጆችን ተነሳሽነት ያሳድጋል፡፡ በተጨማሪም ግጭት አስወጋጅ ሽማግሌዎች ፖሊስ የሚሰጣቸው እገዛ በጣም ደካማ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ሩቅ ቦታ ሄደው ለማስታረቅም በእግራቸው አልያም በራሳቸው የትራንስፖርት ወጪ ተንቀሳቅሰው እየሰሩ ሲሆን ፖሊስ ቢያንስ ሚኪና በመመደብ ወይም በሌላ ሚሊኩ በመደገፍ እገዛ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 8.3. የፀጥታ ሀይሉን ማጠናከር

በየቀበሌው ያሉ የፖሊስ አባላት በተለያየ ጊዜ ህዝቡን ያወያያሉ፤ የወንጀል መከላከል ትምህርትም ይሰጣሉ፡፡ በየቀበሌው ለሚገኙ የሚሊሻ ሀይሎችም በተለያየ ጊዜ ወንጀልን መከላከል እና ተጠርጣሪን ወደ ህግ ማቅረብ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎች እየተሰጣቸው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የሰው ግድያን በሚመለከት የነፍስ ግድያ የሚበዛባቸው ቀበሌዎች ተለይተው የፀጥታ ኮንፈረንሶች እንደተካሄዱ እንደሆነ ለሚረዳት ተችሏል፡፡ ነገር ግን የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ላይ በተደጋጋሚ ህዝቡ ተቀጥሮ አለማኘት ችግር ይታያል፡፡ በተካሄዱት የፀጥታ ኮንፈረንሶች ላይ ከወረዳ፣ ከአስተዳደር ፀጥታ፣ ከሚሊሻ ጽ/ቤት፣ እንዲሁም ከራሱ ከፖሊስ ተቋም አመራሩ ወደ ቀበሌ ወርዶ ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ስራ ሰርቷል፡፡ ኮንፍረንሶቹ በተካሄደባቸው አብዛኞቹ ቀበሌዎች ላይ የነፍስ ግድያ ወንጀል ለመቀነስ መቻሉም ታይቷል፡፡ ስለዚህ ማሳል የፀጥታ ኮንፈረንሶችን በሰፊው በማካሄድ በሌሎችም ቀበሌዎች ላይ ወንጀሉን መቀነስ እንደሚቻል ማገንዘብ ይቻላል፡፡ ሰፋፊ መድረኮች ማካሄድ ባይቻል እንኳ አነስተኛ የቡና ጠጡኝ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ግጭቶችን በእንጭጩ ለመግታት ከማህበረሰቡ ጋር መወያየት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ በሞጣ በተወሰኑ ቀበሌዎች ላይ የሰላም ቡና ጠጡኝ ፕሮግራም ተቋቁሞ በየመንደሩ በወር አንድ ጊዜ የአካባቢው ማህበረሰብ የተጣላ ሰው የሚያስታርቁበት፤ የተኳረረፈን ሰው ይቅርታ የሚያባብልበት ስርአት አለ፡፡

የፖሊስን ስራ ለመደገፍ የተዋቀሩት የግጭት አስወጋጅ ኮሚቴ፣ የሰላም ኮሚቴ፣ የወጣት ኮሚቴ እና ሌሎችም አደረጃጀቶች ስልጠና እየተሰጣቸው በቀበሌ ኦፊሰሮች በኩል ለተግባር ይወጣሉ፡፡ በትክክል ወደ ተግባር ስለመግባታቸው እና ስለሰሯቸው ስራዎች በየጊዜው እየተገናኙ ይወያያሉ፡፡ በተጨማሪም ህብረተሰቡን በጥበቃ ቡድን በማደራጀት የቅድመ መከላከል ስራ እንዲሰሩ የፀጥታ ሀይሉን በተመሣሣይ በተቋሙ አደረጃጀት መሠረት ከቀጠና ጀምሮ በቀጠና ኃይል በቀበሌ ኮማንደር ታች ደግሞ ጐጥ ድረስ በቲም በሚል አደረጃጀት ተደራጅተው ማህበረሰቡ የራሱን ፀጥታ እንዲያስከበር ተልዕኮ ተሰጥቶታል፡፡

ነገር ግን እነዚህ አደረጃጀቶች የሰሩትን ስራ በየጊዜው ከማገምገም እና ከመከታተል እንዲሁም ከመደገፍ አንፃር በየቀበሌው ያለው የፖሊስ ኦፊሰር ላይ የአቅም ማነስ

ይስተዋላል፡፡ በዞኑ ባሉ ቀበሌዎች አንዳንድ የቀበሌ ኦፊሰሮች ያሉ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም አንድ አፊሰር ሌሎች ቀበሌዎችን ደርቦ የሚሰራበት ሁኔታ አለ ምክንያቱም አንዳንድ ቀበሌዎች ላይ የፖሊስ ኦፊሰር ስላልተመደበ ወይም በሚለቅበት ጊዜ በፍጥነት ስለማይተካ ነው፡፡ ለምሳሌ እነማይ ወረዳ ላይ ዘጠኝ ቀበሌ ላይ የፖሊስ ኦፊሰር የለም፡፡ በነዚህ ቀበሌዎች ስር የቀበሌ አማካሪ ምክር ቤት አለ፤ ግጭት አስወጋጅ ኮሚቴ አለ፤ የጐጥ ፖሊስ አለ እንዲሁም የቤተሰብ ፖሊስ አለ፡፡ ነገር ግን እነሱን የሚያነቃንቅ ፖሊስ ኦፊሰር የለም፡፡ ያሉት የቀበሌ ኦፊሰሮችም ሁሉንም ጎጦች አዳርሰው ወንጀልን ከመከላከል እና ታች ድረስ የተዘረጉ አደረጃጀቶችን ከመደገፍ አንፃር የአቅም ማነስ ይስተዋልባቸዋል፡፡ በመሆኑም የፀጥታ ሀይሎችን ቁጥር በመጨመር ፖሊስ ለማህበረሰቡ ያለውን ተደራሽነት ማጎልበት ይቻላል፡፡ መንግስት ተጨማሪ የሰው ኃይል አሰልጥኖ ለቀበሌዎች አንድ አንድ ፖሊስ እንዲዳረስ ማድረግ አለበት፡፡ ይህም ከኮሚኒቲ ፖሊሲንግ አደረጃጀቶች ጋር በመሆን አደረጃጀቶቹ የሰውግድያ ወንጀልን ለመቀነስ የሚሰሩትን ስራ በመደገፍ የሰውግድያ ወንጀልን መቀነስ ያስችላል፡፡

ይህን የፖሊስ ስራ ህዝባዊ ማሳረት ከማስያዝና ወንጀልን የሚጠየፍ ማህበረሰብ ከመፍጠር አንፃር ሰፊ ስራ ይጠበቃል፡፡ ፖሊስ ተሯሩጦ ወንጀለኛን እንዲይዝ ከማድረግ ባሻገር የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት ወንጀልን ከምንጩ ለማድረቅ ሰፊ የመከላከል ስራ ማስራት ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም ፖሊስ ከሽማግሌዎች እና ከሀይማኖት አባቶች ጋር በመጣመር የአመለካከት ለውጥ በማምጣት ወንጀል ጠል ማህበረሰብ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ አንድ የፖሊስ አባል አንድ አካባቢ ላይ ሲቆይ ከህብረተሰቡ ጋር ይላመዳል፡፡ ይህ በአንድ በኩል የማህበረሰቡን ችግር ለይቶ ከማወቅ አንፃር መልካም ቢሆንም አጉል ልማዶችን እና አስተሳሰቦችን ከመቀየር ይልቅ በዛው አስተሳሰብ ተውጠው ይገኛሉ፡፡

በዞን እንዲሁም በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የፀጥታ አካላት በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ወንጀሎችን መንስኤ ለማየትና መፍትሄ ለሚፈለግ ጥናትና ምርምሮችን ያደርጋሉ፡፡ በተለይም በቀበሌ ደረጃ በነዚህ ጥናቶች ላይ በመመስረት የማስተማሪያ ማንዋሎችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በሰላም ቡና ጠጡ ፕሮግራሞች ላይ እየተሰጠ ይገኛል፡፡ ነገር ግን ህብረተሰቡ ቀኑን አውቆ ያለቀስቃሽ እንዲመጣ በማድረግ በኩል ክፍተቶች ይታያሉ ብሎም ህብረተሰቡ መደበኛ በሆኑ ሰብሰባዎች ላይ የማሳተፍተነሳሽነቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለዚህ እንደአማራጭ እድር፣ ማህበር እና ቤተክርስቲያንን የማሳሰሉ ህብረተሰቡ ያለቀስቃሽ የሚገኝባቸውን መድረኮች መጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ ካለ ማጤን ያስፈልጋል፡፡

በየጊዜው ግንዛቤ ለማስጨበጫ እና ለተለያዩ አላማዎች በፀጥታ አካላት የሚጠኑ ጥናቶች አበረታች ሆነው ሳለ የወንጀል መንስኤን በአግባቡ የሚለዩ፤ በሳይንሳዊ የጥናት ዘዴ

የተደገፉ እና ዘላቂ መፍትሄ ማቅረብ የሚችሉ እንዲሆኑ በጥናቶቹ ለሚሳተፉ አባላት በቅድሚያ ማስረታዊ የጥናት እና ምርምር ስልጠና ማስጠት አስፈላጊ ሲሆን ለዚህም ደብረ ሞርቆስ ዩንቨርሲቲ እና የዞኑ የፀጥታ አካላት በጥምረት ማስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጥናቱን ለሚያካሂዱት የፀጥታ አካላት ብቻም ሳይሆን ጥናቶችን ማስረት አድርገው ታች ነጥ ድረስ ወርደው የግንዛቤ ማስጨምጫ ለሚሰጡ የፀጥታ አባላት ተገቢው የህግ፣ የባህል፣ የስነ-ልቦና እና ሌሎች ተማሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በዞን ደረጃ የወንጀል ሁኔታን በተከታታይ የሚያጠና የምርምር ተቋም አቋቁሞ ከደብረ ሞርቆስ ዩንቨርሲቲ ጋር በመተባበር በተለያየ ጊዜ የሚያጋጥሙ የወንጀል ተግዳሮቶችን እና የኮሚቴ ፖሊሲንግን የአሰራር ክፍተቶች እያጠና የመፍትሄ ሀሳብ ሚፈላለግ ያስፈልጋል፡፡

የዞን ፖሊስ፣ ፀጥታና ሚሊሽያ ፅ/ቤቶች በየጊዜው የሰው ግድያ ወንጀልን እንዲሁም ምክንያት የሚሆኑት ግጭቶችን መቀነስ ላይ ያተኮረ ንቅናቄ በመፍጠር ታች ቀበሌ ድረስ ያለውን የፀጥታ ሀይል እንዲነቃቃ ሟድረግ ይችላሉ፡፡ ከቡድን ተኮር ውይይቶች ሞረዳት የተቻለው የፀጥታ ሀይሉ ቀዝቀዝ ባለበት ጊዜ ስርቆቶች፣ ድብደባዎች እና ግድያዎች እነደሚበራከቱ እና የፀጥታ ሀይሉ እንደ አዲስ በሚነቃቃበት እና በሚንቀሳቀስበት ወቅት ደግሞ የወንጀል ድርጊቶች በከፍተኛ ሁኔታ የመቀነስ ሁኔታ እንደሚያሳዩ ነው፡ በአመት እቅድ ውስጥ በማካተት በየ3 ወሩ አልያም በየ6 ወሩ ማህበረሰቡን የሚያሳትፍ የወንጀል መከላከል ንቅናቄ ማካሄድ ለጊዜው የወንጀል ድርጊቶችን ከመቀነስ ባለፈ በዘላቂነት ወንጀል ጠል፣ ግጭትን በሰላማዊ ሜኪኑ መፍታትን የሚሞርጥ የሰለጠነ ማህበረሰብ ለመፍጠር እንደማሻ ያገለግላል፡፡ ነገር ግን ወንጀልን በዘላቂነት ለመቀነስ በቁጥጥር እና በጥበቃ ላይ የተማሰረተ አሰራር አዋጪ አይደለም ምክንያቱም ወንጀል በተለይም የሰው መግደል ማህበራዊ ክስተት በመሆኑ በአጋጣሚ ሊከሰት የሚችል ነው፡ በመሆኑም የሚሰሩ የንቅናቄ ስራዎች ህብረተሰቡ ላይ ዘላቂ የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣትን አላማ ያደረጉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡

የፀጥታ ሀይሉ የተጣለበትን ሀላፊነት በብቁ ሁኔታ እንዳይወጣ ማነናክል ተደርገው ከተነሱት ማነናክሎች ማካከል አንዱ የበጀት እጥረት ነው፡ በቀጠና ደረጃ ሥልጠና ለማስጠት የግጭት አስወጋጅ ኮሚቴ ሰብሣቢ ፣ የሐይማኖት አባቶችን ፣ የቀበሌ ዋና አስተዳዳሪዎችን ፣ አስተዳደር ፀጥታ ኮማንደሩን እያሰባሰቡ የጋራ እቅድ ለመንደፍ እና በየጊዜው እየተገናኙ ለመገምገም የበጀት እጥረት እንዳለ ተጠቁሟል፡፡ በመሆኑም የታችኛው የፀጥታ መዋቅር ድረስ የበጀት ማሻሻያ ተደርጎ የሚመለከታቸው አካላት የተቀናጀ የፀጥታ ማስከበር እና የግጭት መቆጣጠር ስራ እንዲሰሩ ሞርዳት ያስፈልጋል፡፡

## 8.4. የህብረተሰብየአማካከት ለውጥላይ ማስራት

የማህበረሰቡ ለምን ተነካው እና አልሸነፍ ባይነት ከየትኛውም የግድያ ምክንያቶች ጋር በጥምረት ሙታየት አለበት፡፡ በድርጊቱ ከሚደርስበት የህግ ቅጣት እና ሌሎች ውጤቶች ይልቅ ተነክቷል ብሎ የሚያስበውን ክብሩን በሚያስበልጥ ማህበረሰብ ውስጥ ወንጀልን ለመከላከል ቅጣትን ከማስደግ በላይ ድርጊቱ ተጎድቷል ብሎ የሚያስበውን ክብር እንደሚያስሚልስለትና ይልቁንም በድርጊቱ የሚጠፉ እና የሚጎዱ ብዙዎች እንዳሉ በጥልቀት ማስተማር የተሻለ የወንጀሉን ድርጊት የመቀነስ አቅምአለው፡

በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የአማካከት ለውጥ ማምጣት በአንድ ሌሊት ሊሳካ የሚችል ባለመሆኑ ተከታታይ፣ በተግባር የተደገፉ እና ሁሉንም ያሳተፉ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ሊተገበሩ ይገባል፡፡ ከነዚህምመካከል የሚከተሉትን እርምጃዎች መተግበር ያስፈልጋል፡፡

- የሰው ግድያ ወንጀል ላይ የተሳተፈን ሰው ማህበረሰቡ በግልፅ እንዲያወግዝ እና በተለያየ ሚዲኩለድርጊቱ ተቃውሞውን እንዲገልፅ ማድረግ፤
- በሟች ቤተሰብ ላይ የደረሰውን ጉዳት፣ ገዳይ እና ቤተሰቡምያጡትን ነገር በተለያዩ መድረኮች እንደማሳያ እያነሱ ማህበረሰቡነግ-በእኔ የሚል እሳቤ እንዲይዝ ማድረግ፤
- የማህበረሰቡን አማካከት ልሙታዊ እና ወንጀል ጠል ለማድረግ የሚያስችሉ የባህል ጥናቶች ከደብረ ማርቆስ ዩንቨርሲቲ እና ሌሎች አጋር አካላት ጋር በጋራ ማስራት፤
- ከማህበረሰቡየወጡተፅዕኖ ፈጣሪ ግለሰቦችን እና ምሁራንን ተሰሚነታቸውን በማጠቀም ከተለያዩ ቦታዎች በማሰብሰብ ማህበረሰቡ ድረስ ወርደውእንዲያወያዩ ማድረግ፤
- የክልሉ ትምህርት ቢሮ የማህበረሰቡ ልዩ ችግር የሆኑትን በማየት ከመጀመሪያ ደረጃ አንስቶ በስነ ዜጋ ትምህርት ካሪኩለምውስጥእንዲካተት ማድረግ፤
- በተለየ ሁኔታ የሰውግድያን መቀነስ የቻሉ ቀበሌዎችን ለይቶ ማበረታቻዎችን ማድረግ፤ ልምዳቸውን ለሌሎች ቀበሌዎች እንዲያካፍሉ መድረኮችን ማዘጋጀት፤
- ከታራሚዎች ጋር በተደረጉ ቀላ ማጠይቆች በተማሳሳይ ሲነሳ የነበረውሀሳብበእስር ላይ ሆነው ሲያስቡት ወደ ግጭት/ጥል ከማምራት ይልቅ ወደ ህግ ባሙራሁ ኖሮ የሚል ፀፀት ነው፡ በሙሆኑም ህብረተሰቡ ለታራሚው ያለውን አማካከት እንዲቀይር በማድረግ ታራሚዎች በሚማሩ ቤት ውስጥ የተማሩትን ትምህርት፣ በሙታሰራቸው እነርሱ እና ቤተሰባቸውያጣውን ለህብረተሰቡእንዲያካፍሉ ማስቻል፤
- የደብረ ማርቆስ ማህበረሰብ ሬድዮ ከህግ ትምህርት ቤት ጋር በሙተባበር ያለውን ተደራሽነት በማጠቀምበቋሚነት የሰውግድያ ወንጀል በሟች ቤተሰብ፣ በገዳይ ቤተሰብ ብሎምበማህበረሰቡላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተፅዕኖ ማስተማር፣

## 9. ማጣቀሻዎች

UnivUniversal Declaration of Human Rights (1948).

International Covenant on Civil and Political Rights (1966).

United Nations (1982). *Office of the High Commissioner for Human Rights General Comment No. 06 The right to life (article 6).*

CDC (2012). *National Center for Injury Prevention and Control, Web-based Injury Statistics Query and Reporting System*. በድረ ገፅ የሚገኝ http://wisqars.cdc.gov:8080/costT/.የካቲት 13/2009 እንደተጎበኘው

የኢፌዲሪ ህገመንግስት (1987).

አያሌዉ አባተ (2007). ደም መቃባት በምስራቅ ጎጃም ዞን. ያልታተመ.

Mekonnen Nigusie and Aberha Melese (2009). *Perjury in East gojjam zone*. Unpublishedersal Declaration of Human Rights፣ 1948